# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሣን *


## የት ደርሰናል? ተስፋና ስጋት ሲመዘኑ


ቅጽ 46፣ ልዩ ዕትም ግንቦት 2010


አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሦስት ዓመታት ሲንጣት የነበረው ሕዝባዊ ወጀብ ጋብ ብሎ በአንድ በኩል ተስፋን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስጋትን የሰነቀ ጊዜ ላይ ደርሰናል። ይህ ሕዝባዊ ትግል ወደ ሥልጣን ያመጣቸው አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ እስካሁን በተናገሯቸው ቃላት ተስፋን የፈነጠቁ ሲሆን ስጋቱ ደግሞ ሄደው ንግግር ባደረጉባቸው ቦታዎችና በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ አሁንም ችግሮች እያመረቀዙ በመቀጠላቸው በሕዝቡ በኩል ቃል ከግብር ይዋሃድ ይሆን? የሚለው ጥያቄ በፖለቲካው ድባብ ላይ ያጠላ መሆኑ ነው።

በመጀመሪያ በኅበኙት የ"ሶማሌ ክልል" በሚባለው አካባቢ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ከመኖሪያቸው በመፈናቀላቸው የችግሩ ሰለባ በሆኑት የኦሮሞ ተወላጆችና በሶማሌ ኢትዮጵያውያን መካከል ዕርቀ-ሰላም የማውረድ ዓላማቸውን ጨርሰው እግራቸው አካባቢውን ከመልቀቁ፣ ችግሩ እንደገና ማገርሸቱ ብቻ ሳይሆን ሌላ ተጨማሪ ችግርም በመከሰቱ የኢትዮጵያ ሶማሌዎች የ"ክልሉን አስተዳዳሪ" (ገዥውን ማለት ይቀላል) የአብዲ ኢሌን ኢ-ዴሞክራሲያዊ፣ ወገናዊና በሙስና የተበከለ አገዛዝ በመቃወም ከጊዜ ጊዜ፣ ከከተማ ከተማ እየተስፋፋ የመጣ ሕዝባዊ ተቃውሞ መከሰቱ ነው። ይህ የዘርና የቋንቋ ፌደራሊዝም በአገሪቱ ያመጣው ጣጣ በዚህ አካባቢ ብቻ አላበቃም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጥለው በኅበኙት በትግራይ መቀሌ ከተማም ለገጠማቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፣ የወልቃይትን ግዙፍ የማንነት ጥያቄ የዲያስፖራ ሜራ በሚያስመስል መልክ በመመለሳቸው የፈጠረው ቅሬታና ችግር ጎንደርና ባህር ዳር ድረስ ተከትሏቸዋል። ጎንደርም ላይ ምንም እንኳን የወልቃይትን ጥያቄ እንዲመሩና መፍትሂ እንዲያፈላልጉ ከፍተኛ የሕዝብ ድምፅ በማግኘት ከተመረጡት መካከል ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ሆን ተብሎ

እንዳይገኙ ቢደረግም፣ ሌሎቹ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ከጠቅላይ ሚኒስትሩና አጋሮቻቸው ጋር በወልቃይት ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አድርገዋል። ኮሚቴው ፍትህ እንደሚሻና ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉ አቤቱታውን ማሰማቱ እንደተፋት ተቆጥሮበት አባላቱ በህወሓት አምባገነን መሪዎች ወደ እሥር ቤት እንደተወረወሩና እንደተሰቃዩ አገር የሚያውቀው ጉዳይ መሆኑን አውስተው፣ ዛሬም ጥያቄው የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የአጋሮቻቸውን መልስ እንደሚጠብቅ አስታውሰዋቸዋል።

ከትግራይ ቀጥለው በጎበኙት አምቦ ከተማም እንደዚሁ የቄሮን ወጣት ትግል እሳቸውና ምክትላቸው በሚያስደምም ሁኔታ በስም ጠርተው ዘክረዋቸዋል። ታዲያ ከላይ እንደጠቀስነው፣ እዚህም እግራቸውን ከማንሳታቸው በአምቦና በጎረቤቷ በጊንጪ የአረማያ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው እንዲፈቱና የአግዓዚ ጦር ግቢያቸውን ለቅቆ እንዲወጣ ተከታታይ ሰልፎችን አድርገዋል። ብዙም ሳይሰነብት የሻኪሶ ከተማና የአካባቢው ሕዝብ ሚድሮክ የወርቅ ማምረቻ ድርጅት ለሌላ 10 ዓመት የተሰጠውን ወርቅ የማውጣት ውል በመቃወም እስካሁን ያልበረደና በክልሉና በፌደራል መንግሥቱ መካከል ልዩነት ያለ የሚያስመስል ከፍተኛ ሕዝባዊ አመፅ ተቀጣጥሏል። የሕዝባዊው አመጽ ምክንያት የወርቅ ማዕድኑ የአካባቢውን አየር፣ አፈርና ውኃ በመበከሉ ሳቢያ በአካባቢው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የጤና መታወክ እያደረሰ ያለ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የአካባቢው ወጣቶች የወርቅ ማዕድኑ ለአካባቢያችን ምንም አልተጠቀመም የሚል ስሞታም አላቸው።

ቀጣዩ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉብኝት ሃዋሳ ነበር። እዚያው በጉብኝት ላይ እያሉ በጉጂ ኦሮሞዎችና በጌዲኦ የደቡብ ክልል ኗሪዎች መካከል መጀመሪያ በመቶዎች ቆይቶ ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ያፈናቀለው የርሰ በርስ መናቆር ህወሓት ያመጣው የዘር በሽታ አካባቢውን እያመሰውና የተጎጂዎቹንም ቁጥር ከፍ እያደረገው ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ ችግሩ ከዘር ግጭት አልፎ በአዋሳ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ የኦርቶዶክስ ተማሪዎች መብታችን አልተከበረም፣ ለሕይወታችን እንሰጋለን ብለው በቤተክርስቲያን ውስጥ እስከመጠለል ደርሰው ነበር።

ይህ በዓይነቱ በርካታና መጠነ ሰፊ የዘር ብጥብጥ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሲሄዱም ተከትሏቸዋል። አማራዎችን መጤ በማለት በተደጋጋሚ ከዚህ በፊት በዚህ ክልል የተሰራው የማፈናቀል ወንጀል እንደገና አገርሽቶ በአሁኑ ዙር ደግሞ ቁጥራቸው ከ500 በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው ባህር ዳር ከተማ አይዟችሁ ባይ መንግሥታዊ አካል አጥተው፣ ከአንድ መጠለያ ወደ ሌላ መጠለያ በመንከራተት ላይ ናቸው። የአማራው

መንግሥት ተብየውም "አላውቃችሁም፤ ወደ መጣችሁበት ሂዱ" ሲላቸው፣ ወደመጡበት እንዳይመለሱ ደግሞ አፈናቅለው፣ ንብረታቸውን ወርሰውና በሕይወታቸው ዝተው ያባረሯቸው ወንጀለኞች ስላሉ አጣብቂኝ ውስጥ ሆነው ከተቆርቋሪ ወገንና ከቤተክርስቲያን ምፅዋት እየተለገሳቸው በብርድና በሃሩር በመንገላታት ላይ ናቸው ።

ይህች ኢትዮጵያ ነች እንግዲህ ይህን ከላይ ያወሳነውን ተስፋ ልትደፍቅ እጆቿን ዘርግታ ሁከትና ብጥብጥን ከህወሓት ወርሳ በዚህ መንገድ 27 ዓመት በለመድኩት ልሂድ ወይስ አዲስ ጎዳና ልቀይስ? እያለች ከራሷ ጋር የምትታገለው።

ለነገሩ ችግሩ መቼ የፖለቲካ ብቻ ሆነና! ስንቱ ተነክቶ?

በኢኮኖሚው ዘርፍ ሕዝቡ የዕለት ጉርሱን ቢያገኝ ኖሮ ዝም ብሎ ተከድኖ ይብሰል ይል ነበር። ሾላ በድፍን ነውና። ነገር ግን የኑሮ ውድነቱ ከማስመረር አልፎ ረሃብተኝነትን በሠራተኞች ላይ ጭምር እያስፋፋ ነው። የአንድ የፋብሪካ ሠራተኛ በአማካይ 650 ብር ያገኛል። የቤት ኪራይ አዲስ አበባ ውስጥ ሁለት ክፍል ያለው ኮንዶሚኒዮም ከ4000 ብር በታች አይገኝም። ምን በልቶ ነው ከወር እስከ ወር የሚደርሰው? እንኳን ቤተሰብ ያለውና ወንደላጤም በዚህ ደመወዝ በቀን ከአንድ ምግብ በላይ መመገብ አይችልም። ከአሠሪውና ከአገዛዙ ጋር ተደራድሮ ደሞዙን እንዳያስጨምር በሙስና የተጨማለቁ ባለሥልጣናትና መንግሥት ተብየዎች "የሠራተኛ ማኅበር ምን ሲባል ታስቦ"? የሚሉ ጉዶች ናቸው። እንደ ደርጉ ዘመን ወደ ኅብረት ሱቆች ጎራ ብሎ ስኳርና ጨው መግዛት እንኳን ለብዙዎች ቅንጦት የሆነበት ጊዜ ሆኗል።

ይህ ችግር እንግዲህ ሥራ ላለው መሆኑ ነው። ለሥራ አጡ በተለይም ለወጣቱ ደግሞ የትዬለሌ ሆኗል፣ የት ተውሎ? ምን ተበልቶ? ለዚህም ነው ከእነሱ የቀደሙት ወጣቶች በደቡብ አፍሪካ አገሮች እስር ቤቶች እንደታጎሩ፣ በሜዲትራኒያን የባህር የአሣነባሪ ሲሳይ እንደሆኑ፣ በሲናይ በረሃ እንደሞቱና እንደተንገላቱ እያወቁና በዐረብ አገሮችም ግፍ እንደሚደርስባቸው እየተገነዘቡ፣ አገራችን ምድር ላይ በረሃብ ከምናልቅ፣ የሰው አገር በረሃና ባህር ይብላን ብለው የሚሰደዱት ።

ከተሜውና ወጣቱ እንዲህ ሲንገላታ፣ ገጠሬውና አርብቶ-አደሩ ደግሞ በድርቅና በረሃብ ይንገላታል። ቁጥሩ እስከ8 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ በረሃብ አደጋ በመሰቃየት ላይ እንደሚገኝ አገዛዙና የምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች ይፋ ያደረጉት አሃዝ ነው። የቤት እንሣቱ

እየሞቱበት፣ የሚያገኟት ምጽዋት በበቂ አንጀቱን ሳትመልስ የሚሰቃየውን የሰው ብዛት ደግሞ ቤቱ ይቁጠረው።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ በአፍሪካ የውኃ ማማ ተብላ የምትታወቀው የባለ ብዙ ወንዞች፣ ተፋሰሶችና ሃይቆች ባለቤት የሆነችው አገራችን በአገዛዙ የነቀዘ አስተዳደር ምክንያት እስካሁን በታሪኳ በቂ ንጹህ የመጠጥ ውኃና መብራት ለዜጎቿ ለማቅረብ አለመቻሏ ነው። ይህ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪም ነው። አንዳንድ በተፈጥሮ ውኃ የአልታደሉ አገሮች ምድረ-በዳውን ወደምድረ-ገነት እንደለወጡት ይነገራል። እኛ ግን "የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው" ሆነናል። ተሰሩ የተባሉት ግድቦች ለመብራት ኃይል ማመንጫነት ብቻ እንጂ ለእርሻና ለመስኖ ውኃ አገልግሎትና ለንጹህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን እቅዶች ያካተቱ አይደሉም። ለዚያውም "ራስ ሳይጠና ጉተና" እንደሚባለው በአገራችን በየጊዜው መብራት እየተቋረጠ ወደ ጎረቤት አገሮች ለውጭ ምንዛሬ ሲባል የመብራት ኃይል ይሸጣል።

በሌላ በኩልም እንደዚሁ ይህን ምስኪን ሕዝብ እየዘረፉ በድሎት የሚኖሩ በዱባይ፣ በቻይናና በአውሮጳ ባንኮች የሰፌውን ሕዝብ ገንዘብ ሰርቀው የሚያሸሹ በርካታ ባለሥልጣኖች ዛሬም ማንም ዝምባቸውን እሽ የሚል ባለመኖሩ የንብረት ዝርፊያውን ከምን ጊዜውም በበለጠ አጧጡፈውታል። በዋነኛነትም የህወሓት ድርጅቶች፣ ማለትም፣ ኤፈርት፣ ማረትና የብረታብረትና መሃንዲስነት ኮርፖሬሽኑ ማቴክ ጊዜ ሳይፈጅ ባስቸኳይ በገለልተኛ የሙስና ኮሚሽን ሊታዩና ሊመረመሩ የሚገባቸው ድርጅቶች ናቸው።

ይህ ነው እንግዲህ የህወሓት ልማታዊ መንግሥት ተብየው ያተረፈልን ቅርስ። ከ70% በላይ የሆነውን ሕዝባችንን አቆርቁዞና ተስፋ አሳጥቶ ጥቂት የሚንደላቀቁ ሌቦችን በገዥነት ሽፋን የሚያሽሞነሙን ሥርዓት የቆመበት። ተጠያቂነት የሚባል መርህ-ቃል በህወሓት/ኢህአዴግ ታይቶ አይታወቅም። ይባስ ብሎም በሙስናና በችሎታ ማነስ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸውን የወያኔ አሽቃባጮች በሕግ ተጠያቂ መሆን ሲገባቸው፣ ተገላቢጦሽ ሌላ ቦታ በሹመት ሲዛወሩ ይስተዋላል። የአግዓዚ ጦር ከፍተኛ መኮንኖች ገና ለአቅም አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናትን እየገደሉ፣ ይባስ ብለው አንዳንዴም እናቶቻቸው እንዳያለቅሱ እያገዱና በልጆቻችቸው ሬሳ ላይ እንዲቀመጡ እያስገደዱ፣ ሕዝብን ሲያሰቃዩ በገሃድ እየታየ በእነሱ ላይም ምንም አልደረሰባቸውም፤ አይደርስባቸውምም። የወህኒ ቤት ገራፊዎች የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን አባለ-ዘር በማኮላሸት፣ ጥፍር እየነቀሉ በማሰቃየትና ሴት እህቶቻችንና እናቶቻችንን እርቃነ-ሥጋቸውን እንዲቆሙ በማድረግና ወንድ እስረኞች እንዲያዩዋቸው በማስገደድ፣ የሃይማኖት አባቶችምን ቢሆን የምንኩስና አልባሳታቸውን

በማስወለቅ ከባህልና ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት ውጪ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን የፈጸሙትም ቢሆኑ ምንም ሲደረጉ አይታይም።

ለእነዚህም በብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ ዙሪያ ተጠያቂነት እንዲኖራቸውና ላጠፉት ጥፋት ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙና ይቅርታ እንዲጠይቁ የሚያደርግ ሥርዓት ባስቸኳይ መፈጠር አለበት።

ማኅበራዊ ገጽታችን ስናይ የትምህርት ደረጃ ከመቼውም በበለጠ አሽቆልቁሎ ወርዶ ይገኛል። ምንም እንኳን አገዛዙ 45 ያህል ዩኒቨርሲቲዎች ሰርቻለሁ ቢልም፣ ብቃት የሌላቸውና “ለስሚ መጠሪያ ቁና ሰፋች” ዓይነት የሚመስሉ ናቸው። ካለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ወዲህ የትምህርት ሥርዓቱም ታውኳል። የማስተማርና የመማር ሂደቱ ተቋርጧል። ህወሓት የበላይነቱን ለማስጠበቅ በሚያደርገው ሙከራ የአግዓዚ ጦር አባሎቹን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ በማስፈሩ ተማሪዎች ይህን ተቃውመው ከግቢያቸው እንዲወጡላቸው በመጠየቅ ላይ ናቸው።

የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የሚል ሕዝብ ባልመከረበት ዕቅድ አፈጻጸም የድሆችን መኖሪያ እያፈረሱ ባዶ ሜዳ ላይ ያለ በቂ ካሣ በትነዋቸዋል። ካሣ ቢሰጥም እንኳን፣ አየር በአየርና በሙስና ጣራ በነካ የቤት ሽያጭ ዋጋ ድሆቹ የትኛውን ቤት ለመግዛት ነው አቅም የሚያገኙት? የግዳቸው ከከተማዎችና ከሚኖሩበት አካባቢዎች ወጥተው አዲስ አበባ አካባቢ ቤተሰባቸውን በትነውና፣ ከሥራቸውም ተፈናቅለው ብዙዎቹ የጎዳና ተዳዳሪ ከመሆን ሌላ አማራጭ አላገኙም። ይህ ድሆችን የማፈናቀል ሤራ በአንዳንዶች አስተያየት የከተማዋን የብሄር ስብጥር በመለወጥ ህወሓት/ኢህአዴግን በሚጠቅም ሁኔታና ባነገበው ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነው ሲሉ ይተቻሉ።

የአገራችን ደኖችም በቃጠሎ እየወደሙ ነው። ባለፈው ዓመት ብቻ በኦሮምያና በደቡብ ክልሎች በሚባሉት አካባቢዎች ከሺህ ሄክታር የሚበልጥ ደን ተቃጥሏል። ሆን ተብሎ ይቃጠሉ ወይም በቸልተኝነት፣ ለዚህ ጥፋት ተጠያቂ የሚሆኑ የአገዛዙ አካላት መኖር አለባቸው። ደኖች የአካባቢ አየር ለውጥን በመከላከል ያግዛሉ። በከርሳቸው የያዟቸው የዱር እንስሳትና አዕዋፋት ወደ ጎረቤት አገሮች በሽሽት እንዳይሄዱ ይከላከላሉ። በህወሓቷ ኢትዮጵያ ግን ይህ ከቶ የሚታሰብ አልሆነም።

የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲሳሳ በመደረጉ የተነሳ ዛሬ ስፓርት ሜዳ በተለይም እግር ኳስ አካባቢ የሚታየው ብሄር ላይ ያተከረ ግጭት በእርግጥ "እኛ ኢትዮጵያውያን ነን?"

የሚያሰኝ ደረጃ ላይ ተደርሷል። የዘር ፌደራሊዝምን ተከትሎ በተዋቀረው የእግር ኳስ ፌደረሽን ቡድኖች፣ አዲግራት፣ ወላይታ፣ መቀሌ፣ አዋሳ ወዘተ... እየተባሉ የክልልን ማንነት በሚያጠናክር ሁኔታ በመዋቀራቸው የግጭት እንጂ የስፖርታዊ ፍቅር ማዕከሎች ሲሆኑ አልታዩም።

ታላቁን የኢትዮጵያን ሐይቅ ጣናን እምቦጭ የተባለ አረም ሲወረውና ሲስፋፋ የአሣ ሀብታችንና በቱሪዝም የሚገኝ ኤኮኖሚያችን ላይ ችግር ሲፈጥር፣ አገዛዙ ችግሩን ለመፍታት በቀደምትነት አልተገኘም። ዲያስፖራ ያሉ ባለሙያዎችና አገር ወዳዶች ምስጋና ይድረሳቸውና አገዛዙን ከእንቅልፉ ቀስቅሰው ቢያንስ አሁን ሁለቱም በጋራ የሚሰሩበትና ችግሩን የሚያስወግዱበት በር የተከፈተ ይመስላል።

ለአገራችን ኤኮኖሚ መድከም አንዱ ምክንያት በህወሓት ልዩ ጥረት አገሪቱ ወደብ አልባ በመሆኗ ለወደብ ኪራይ ለጂቡቲ፣ ለፖርት ሱዳን፣ ለሀርጌሳና ለሞምባሳ የሚከፈለው የውጭ ምንዛሬ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላለች ድሃ አገር ይህ ወጭ ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያውያን ምሁራን "አሰብ የኢትዮጵያ ወደብ ስለሆነች በሰላማዊ መንገድ ጉዳዩን ከኤርትራ ጋር ተወያይተን ካልተፈታ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉዳዩን አቅርበን መርታት እንችላለን" ቢሉም እንኳን፣ የሻዕቢያ ተላላኪ የሆነው ህወሓት ጉዳዩን እያድበሰበሰ ያልተባለውን "የጠረኞች ዕቅድ" እያለ እስካሁን ድረስ ለጉዳዩ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አቆይቶታል። ይባስ ብሎም፣ አሁን አሰብ ለውጭ መንግሥት በኪራይ በመሰጠቷ ችግሩ የኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ ደህንነትና ፀጥታ ላይም አስጊ ሁኔታን እየፈጠረ ያለ ክስተት መሆኑ ግልጽ ነው።

እንግዲህ ከላይ እንዳልነው ተስፋን የሰነቅነው ይህን እየተከማቸ የመጣውን ህወሓትና ፓርቲያቸው ኢህአዴግ የፈጠሩትን የ27 ዓመታት ችግር ሕዝቡ ራሱ እንዲፈታው ሁኔታዎች ይመቻቹለታል በሚል ነው። ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ በር ከፋች እርምጃዎችም ለምሳሌም፣ አሁንም በእሥር ላይ የሚገኙትን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ሁሉ መፍታት፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከሲቪክ ኅብረተሰቡ ጋር ብሄራዊ የመግባባትና የዕርቅ ጉባዔ ማዘጋጀት፣ የመገናኛ ብዙኃን ነፃ ሆነው ጋዜጠኞችና ዜጎች በነፃ የመሰብሰብ፣ የመናገርና የመፃፍ መብቶቻቸው እንዳይገደቡ ማድረግና የበጎ አድራጎት ድጅቶችንና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን በሽብርተኝነት የሚወነጅሉ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አዋጆች ሁሉ እንዲሻሩ ባስቸኳይ ተግባራዊ መሆን አለባቸው።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የተስፋው ውጤታማነት መለኪያዎች ሲሆኑ፣

ስጋቱ ደግሞ አገሪቱን ሰቅዘው የያዟት ችግሮች ውስብስብና ዘርፈ-ብዙ በመሆናቸው እነዚህን ሁሉ ልንፈታቸው እንችላለን ወይ? የሚል ነው። ይሁንና፣ ተስፋውን ሰንቆ አይቀሬውን የትግል ውጣ ውረድ ጉዞ የተያያዘው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ችግሮቹ ይፈቱ ዘንድ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሕዝብ አጋርነታቸውን ያሳያሉ ብሎ ይጠብቃል። ይህ ደግሞ ለወደፊቱ የሚታይና በታሪክ የሚመዘን ይሆናል።

ይህ የተስፋ ዕይታ ባዶ ሆኖ እንዳይቀር፣ ድርጅታችን ኢሕአፓ (አንድነት) ለትግል አዲስ ስላልሆነና በትግሉ ከ40 ዓመታት በላይ የቆየንበት በመሆኑ፣ ለአንድ አፍታም ሳናመነታ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ዕውነተኛ ዴሞክራሲንና ብልጽግና ናፋቂ ከሆኑ መሰል ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመሆን ትግሉን ያፋፍማል፤ ስጋትን አጨልሞ የተስፋ ቀንዲልን ከሕዝብ ጋር እያበራ ወደ ሕዝባዊ የድል ጎዳና ያመራል!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!